



# አራት አመት ቀረው ?!




ዕልባት ሳያገኝ ለአምናው መቋጫ፣
አራት ዓመት ቀረው ? ተከታዩ «ምርጫ»፤

እንደው ባጋጣሚ እማይሆነው ሆኖ፣
አራት ዓመት ቢደርስ - ታምቆ ታፍኖ፤
ምን ልትል ነው ቪኪ? ምን ሊል ያማሞቶ፣
የማያልቀው ተዓምር ጉዳቸው ተሰምቶ።

ሊደግሙልን ይሆን ችክ ያለ ትያትር፣
የክህደት፣ የሃሰት... ባለ ሦስት ገቢር፤
ምን ሊባል ነው ሕዝቡ ? ግፍ የተሰራበት፣
«ፍትህ፥ ዲሞክራሲ ... ባስገኙልህ ድል መብት»
«ለሁሉም ጊዜ አለው» ዳግም ወተህ ምረጥ ???

ያ! ቀዳዳ ሳጥን ዳግም ተገትሮ፣
አግአዚ ሚልሻ ብረቱን ወድሮ፤
የዜጎች ንጹህ ደም ከንቱ ተገብሮ...።
የሕዝቡ ላብ - ጥሪት በሃሰት ተከስክሶ፣
ክቡር ጂሚ ካርተር ነጭ - ልብሱን ለብሶ፣
በደም ላይ ተራምዶ ሃቁን አድበስብሶ፤
ትዝብቱን ሊታዘብ ህሊናውን አስታሞ፣
ለሁለተኛ ኖቤል ሊታጭብን ደግሞ ?!

እንዴት ሊደረግ ነው ? እኔንስ ጨነቀኝ፣
የሰውነት ክብርን ህሊናን ሸቅጦ፣
ለወቅታዊ ጥቅም ሆድን ለብር ሸጦ፣
በሚኖር ከንቱ ዓለም - መኖሩ ታከተኝ !!!

አብርሃም ሊንከን ነው ?
የራሳቸው ዜጋ - ምሳሌ የነገረው ?
«ሕዝብን አንድ ጊዜ - ቢበዛ ሁለቴ፣
ማታለል ይቻላል፤ አይሆንም ግን ሦስቴ»
ማሰለስ ሙከራ ሕዝብን ለማሞኘ፣
የቁም ቅዠት እንጂ አይሰምርም ዳግመኛ !!!

ጌታቸው አበራ
ሚያዝያ ፲፱፻፺፰ (1998)

